# የግንቦት 7 ድምጽ

የግንቦት 7 የፍትሕ፣ የነፃነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ፤ ሳምንታዊ ልሳን

www.ginbot7.org

አንብበው ያስነብቡ! አባዝተው ያሰራጩ!

ቁጥር 216 ሰኔ 28 2004 ገጽ 1


ለእነ አቶ አንድዓለም ጥሪ የግንቦት ምላሽ የሚከተለው ነው፡፡

*የመለስ ዜናዊ አገዛዝ መወገድ ይኖርበታል። የፍልሚያ ስልትም የሚመርጥልን እሱ አይደለም። በተመቸን መንገድ ሁሉ ተጉዘን አገዛዙን እናስወግዳለን።*

በግንቦት 7 እምነት፣ በወያኔ መዳፍ ውስጥ ያሉ ወገኖቻችን በእስር ላይ የሚቆዩበት የስቃይና የመከራ ዘመን የእኛ - ኢትዮጵያዊያን - የመከራና የስቃይ ዘመን ነው።

ከግንቦት 7 ዕርሰ-አንቀጽ የተወሰደ (ገጽ-2)

## በአፋር ክልል ቀይ ሽብር ተጀመረ። በትናንትናው እለት ሁለት የክልሉ ተወላጆች ከእስር ቤት ተወስደው ከተረሸኑ በኋላ አስከሬናቸው አደባባይ ላይ ተጥሏል

የአፋር ሰብዓዊ መብት ድርጅት ሊቀ መንበር አቶ ጋአስ አህመድ ከግንቦት 7 ሬዲዮ ጋር ባደረጉት ቃለምልልስ እንደገለጹት አቶ መሃመድ ሀቲና አቶ ሃሰን ከቢር የተባሉት አፋሮች ሰሞኑን በክልሉ ባልታወቁ ሰዎች ከተገደሉት ሁለት የፖሊስ አባላት ጉዳይ ጋር በተያያዘ ለምርመራ በክልሉ ፖሊስ ተይዘው ከታሰሩ በኋላ የፌደራል ፖሊስ አባላት ሌሊት ወደ ክልሉ ፖሊስ ጣቢያ በመሄድ አስገድደው ይወስዷቸዋል፤ ከዚያች እለት ጀምሮ ሁለቱ ዜጎች የት እንደደረሱና ምን እንደደረሰባቸው ሳይታወቅ ሰንብቶ ቤተሰብ እንዲጎበኛቸው ጊፊት ሲያበዛ ከትናንት በስቲያ ሰኞ ሁለቱንም ታሳሪዎች ገድለው የክልሉ ቢሮ ፊት ጥለዋቸዋል።

አቶ ጋአስ እንደሚሉት ይሄ ርምጃ በአሁኑ ወቅት እስር ቤት ውስጥ በሚገኙ ሌሎች ዘጠኝ አፋሮች ላይ እንደማይቀጥል ምንም አስተማማኝ ነገር የለም። ህዝቡ በከፍተኛ ደረጃ መቆጣቱን የገለጹት አቶ ጋአስ በቀይ ሽብር ማስፈራራት ለደርግም አልበጀው፣ የወንድሞቹ ሬሳ ሜዳ ላይ ተዘርሮ ማየት የአፋርን ህዝብ ለበለጠ ትግል ከማነሳሳት ውጪ ወያኔ እንደሚያስበው አንገቱን አያስደፋውም ብለዋል ።

የአፋር ክልልን መሬት በልማት ስም ለኢንቨስተሮች ለመቸብቸብ እየተደረገ ያለውን፣ ከፍተኛ የወያኔ እንቅስቃሴ አምርሮ እየተቃወመ የሚገኘው የአፋር ህዝብ ንቅናቄ ስጋት ላይ የጣለው ዘረኛውና ስግብግቡ የወያኔ መንግስት ህዝቡን ለማሸማቀቅና አንገት ለማስደፋት የሚችለውን እኩይ ድርጊት ሁሉ እፈጸመ ይገኛል ሲሉም አክለዋል። (ወደ ገጽ 2 ዞሯል)

## የወያኔ ጉዳይ ፈጻሚ የሆነው የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት 3ኛ ወንጀል ችሎት በእነ አንዱ ዓለም አራጌ የክስ መዝገብ ላይ የሰጠውን የጥፋተኝነት ውሳኔ አንድነት ለፍትሕና ለዴሞክራሲ ፓርቲ (አንድነት) አጥብቆ እንደሚቃወም በሰጠው ጋዜጣዊ መግለጫ አስታወቀ

መግለጫውን ጠቅሶ የዘገበው ፍትህ ጋዜጣ እንዳለው ፓርቲው መግለጫውን የሰጠው በሀገራችን የፍትህ ተቋማት እንደማጥቂያ መሳሪያነት እንዳያገለግሉ፣ ህወሓት/ኢህአዴግን በሕጋዊ ትግል ከስልጣን ማስወገድ አማራጭ የለውም በሚል ርዕስ ነው ።

ፓርቲው በዚሁ ወቅት፣ መለስ በተለያዩ አጋጣሚዎች የታሳሪዎችን ጥፋተኝነት በአደባባይ የተናገረውን ፍርድ ቤቱ በጽሁፍ አንብቦታል ሲል ውሳኔው አስቀድሞ በአምባገነኑ መለስ ዜናዊ የተወሰነ መሆኑን አመላክቷል። የፍርድ ቤቱ ወሳኔ ፍርድ ቤቶች ነፃነት የሚባል ነገር የሌላቸው ተቋሞች መሆናቸውን ከማሳየት ያለፈ ፋይዳ እንዳልነበረው የጠቀሰው መግለጫው፣ የፍትሕ ተቋማት ህወሓት/ኢህአዴግ በስልጣን እስካለ ድረስ ነፃ ሊሆኑ እንደማይችሉ ዳግም ያረጋገጠ መሆኑን አስረድቷል።

ተከሳሾቹን ፍርድ ቤት ማቅረብ የተፈለገው ፍትህ እንዲያገኙ ሳይሆን መለስ ዜናዊ በአደባባይ ወንጀለኞች ናቸው በማለት የወሰነባቸውን ውሳኔ ህጋዊ ሽፋን ለመስጠትና በፍርድ ቤት ለማረጋገጥ ነው፤ ይህም ሀገሪቱ በአሁኑ ወቅት አስፈጻሚውን አካል የሚቆጣጠር የመንግስት ስርዓት እንደሌላት በቂ ማስረጃ ነው ብሏል።

በተመሳሳይ ሁኔታ በሽብርተኝነት ሰበብ ተከሰው ውሳኔ በመጠበቅ ላይ የሚገኙት የመድረክ ፓርቲ አመራር አባላት የሚጠብቃቸው ውሳኔ ከዚህ የተለየ ሊሆን እንደማይችል መገመት አስቸጋሪ እንደማይሆንም ፓርቲው አብራርቷል።

በዐቃቤ ህግ መቅረብ የነበረበትን የመከራከሪያ ሀሳብ በችሎቱ ላይ የተሰየሙት ዳኞች "...በአረብ አለም አብዮት የተነሳ በሰዎች ሕይወት ላይ ጉዳት ደርሷል፣ ደም ፈሷል፤ ንብረት ወድሟል" እያሉ ሲያነቡ እንደነበር በመግለጫው ወቅት ተጠቀሶ ይሄ ችሎት ዐቃቤ ሕግ ነው ወይስ የዳኝነት አካል ? የሚለው ነገር ግራ ያጋባ እንደነበር ተብራርቷል፡፡ (ወደ ገጽ 2 ዞሯል)

ግዜ
ግንቦት 7 ዜና

## ሰሜን አሜሪካ ዉስጥ ዋሺንግተን ዲሲ ና ዳላስ ዳላስ በኢትዮጵያዉያን አሸበረቀች ዲሲ የሰዉ ያለህ አለች

በየአመቱ ሰሜን አሜሪካ ዉስጥ የሚካሄደዉ አመታዊዉ የኢትዮጵያዉያን የእግርኳስ ዉስድድር ባለፈዉ እሁድ ሰኔ24 ቀን 2004 ዓም ዳላስ ቴክሳስ ዉስጥ በከፍተኛ ድምቀት ተከፈተ። አንድ ሳምንት የሚቆየዉና ኢትዮጵያዉያንን ከያሉበት በብዛት ያሰባሰበዉ ይህ የስፖርት በዐል በባህላዊ ዘፈኖች፤ በዉዝዋዜና አገራዊ ወኔን በሚቀሰቅሱ ሙዚቃዎችና ትርዕቶች ታጅቦ ከፊት ከፍተኛ ቁጥር ያላቸዉ ኢትዮጵያዉንና የኢትዮጵያን ባህልና ታሪክ የሚወዱ አሜሪካዉያን አድናቆታቸዉን በሆታና በጭብጨባ ገልጸዋል።

በዘረኞች ደባና በመሐመድ አላሙዲ የገንዘብ ሴራ ተተብትቦ ለተወሰኑ አመታት በራሱ መተንፈስ ያቃተዉ የሰሜን አሜሪካዉ የኢትዮጵያዉያን የእግር ኳስ ድርጅት ዘንድሮ የተተበተበበትን የዘረኞች መረብ በጣጥሶ በመዉጣት ዛሬም እንደ ትናንቱ የኢትዮጵያዉያን ንፁህ ድርጅት መሆኑን በተግባር አስመስክሯል። በተለይ የየቡድኑ ተጫዋቾ የሆኑት ብዙ ወጣት ኢትዮጵያዉያን ቡድናቸዉን እንዲከዱ የተከፈላቸዉን ከፍተኛ ገንዘብ አምቢ በማለት ኢትዮጵያዊነት በገንዘብ የማይለወጥ ትልቅ የተዉልድ አደራ መሆኑን ለአላሙዲ ተላላኪዎችና ለአብነት ገ/መስቀል በግልጽ አሳይተዋል። ሰሜን አሜሪካ ዉስጥ የኢትዮጵያዉያን የእግር ኳስ ዉድድር ከዚህ ቀደም 28 ግዜ ተካሂዷል።

የዘንድሮዉን ዉድድር ልዩ የሚያደርገዉ ዘረኛዉ መለስ ዜናዊ በሼክ መሐመድ አላሙዲና በአብነት ገ/መስቀል ተላላኪነት ኢትዮጵያዉያንን በገንዘብ ለመግዛት ያደረገዉን የማማሽ አመት ጥሪ አንቀበልም ያሉ እጅግ ከፍተኛ ቁጥር ያላቸዉ ኢትዮጵያዉያን በእልህ በመነሳሳት ለበጋዉ ወራት የያዙትን ዕቅድ ሰርዘዉ ለአመታዊዉ የእግር ኳስ ዉድድር ዲሲንና ሌሎች ትላልቅ ከተማዎችን እየለቀቁ ዳላስ መጉረፋቸዉ ነዉ። (ወደ ገጽ 4 ዞሯል)

## በኢትዮጵያ የፖለቲካ ምህዳሩ በጣም ጠባብ በመሆኑና መንግስትም ፍቃደኛ ባለመሆኑ በዴሞክራሲ ዙሪያ ድርጅታችው ምንም መስራት እንዳልቻለ ተሰናባቹ የ ዩ ኤስ አይ ዲ ዳይሬክተር ቶማስ ስታል ገለጹ

ዳይሬክተሩ አፍቃሪ ወያኔ ለሆነው ሪፖርተር እንዳሉት ዩ ኤስ አይ ዲ በሌሎች ሀገራት ሁሉም የፖለቲካ ፓርቲዎች አቅም እንዲፈጥሩ፣ አንዱን ከሌላው ሳይለይ አብሮ ይሰራል፤ ስለ ዴሞክራሲያዊ ምርጫ ያስተምራል፤ሚዲያም የምርጫ ሂደቶችን በነጻነት እንዲተነትንና ሀሳብ እንዲሰጥ ድጋፍ ያደርጋል። ይሁንና በኢትዮጵያ እነዚህ ጉዳቶች የተከለከሉ በመሆናቸው በዚህ ረገድ ድርጅታቸው ምንም መስራት አልቻለም።

ወደፊት በዚህ ላይ ለመስራት የተቻለንን ሁሉ እናደርጋለን። ያሉት ስታል ለዚህ ደግሞ የፖለቲካ ምህዳሩ ክፍት መሆን አለበት። ይህ እኛ ስላልን ሳይሆን ለኢትዮጵያም ለራሷ የሚበጃት ስለሆነ ነው ብለዋል።

ከዚህ በማያያዝ ዳይሬክተሩ ለአሜሪካዊያንና ለአውሮፓዊያን ኢንቨስትመንት ኢትዮጵያ ተመራጭ አለመሆንዋን ጠቅሰው ሳቢያውን ደግሞ ስለ ሀገሪቱ ያላቸው የድርቅና የረሃብ መረጃ፣ ለንግድ እንቅስቃሴ አመቺ የሆነ ከባቢያዊ ሁኔታ አለመመቻቸት፣ ዓለምአቀፍ አገልግሎት የሚሰጡ ባንኮች አለመኖር፣ የህጎች ውስብስብነትና የአፈጻጸማቸው አለመገናኘት፣ የቴሌኮም አገልግሎት ክፍት አለመሆንና የመሳሰሉት ናቸው በማለት አብራርተዋል።

ወያኔ መሬት ላይ ያለ ተጨባጭ ሁኔታዎችን ሳያገናዝብ ህዝቡን በባዶ ተስፋ በመሙላት የተቃውሞ ስሜቱን አቀዝቅዥለሁ ብሎ የጫረውን "የትራንስፎርማሽን እቅድ" በማስመልከትም እቅዱ ከአቅም በላይ የሆነና ተስፈኛ ነው። አፈጻጸሙም እንደታሰበው ላይሆን ይችላል። በመሆኑም ለራስ ሀቀኛ መሆን ተገቢነው። የሚመዘገቡ ለውጦችን ከእቅዱ ጋር እያመሳከሩ መከታተልና መመዘን ያስፈልጋል። ይህ ካልሆነ ደግሞ ጉዳዩቹ በታቃደው መሰረት በማይጓዙ ጊዜ እውነታውን መቀበል ያዳግታል ሲሉ ሁሉም ነገር 99 ከመቶ ተሳክቷል ከሚለው ከተለመደው የወያኔ ባህሪ ተነስተው አስተያየት ሰጥተዋል።

የአርብቶ አደሮችን ሰፈራም በተመለከተ ሲያብራሩ ሰፈራ በፈቃደኝነት ላይ የተመሰረተ መሆን አለበት፤ አማራጭ ማቅረብና ሰዎች በነጻነት እንዲመርጡ እድል መስጠት ይገባል። አርብቶ አደርነትና የከብት እርባታ የአገሪቱ ወሳኝ የኢኮኖሚ ዘርፍ ነው። እናም ዘርፉ ጠቃሚ መሆኑን በመገንዘብ ለሰፈራ የሚደረጉ እንቅስቃሴዎች በአግባቡ መገምገም ይገባቸዋል። ምናልባት 10 ከመቶ የሆነውን ገበሬ ማድረግ ይቻል ይሆናል፤ ሁሉንም ገበሬ ማድረግ ግን አይቻልም።ሌሎች አማራጮችንም ማየት ያስፈልጋል። ከተፈለገ እንደ ኬንያና ማሊን ከመሳሰሉ ሀገራት ልምድ መቀሰም ይቻላል በማለት የወያኔን የሰፈራ ፕሮግራም ብልሹነት አሳይተዋል።

## ለእነ አቶ አንድዓለም አራጌ ጥሪ መልሳችን ይህ ነው!

የመለስ ዜናዊ ዘረኛ አገዛዝ በአቶ አንዱዓለም አራጌ መዝገብ ላይ በሃያ አራት ንፁሃን ዜጎች ላይ በርካታ ወንጀሎችን ዘርዝሮ፤ በህገ ወጡ "የፀረ-ሽብር ህግ" ክስ መሥርቶ ሰኔ 20 ቀን 2004ዓ.ም. የጥፋተኝነት ብይን ሰጥቷል።

መለስ ዜናዊ ከፍርድ ቤቱ ቀድሞ ውሳኔውን ተናግሮ ስለነበር የይስሙላ ብይኑ ለብዙዎች አስደናቂ አልሆነም። የመለስ ዜናዊ አገዛዝ ፍርድ ቤቶችን በተቀናቃኞች ማጥቂያ መሣሪያነት የሚጠቀም መሆኑ፤ ዳኞቹም የአገዛዙን ውሳኔ ከማሳወቅ ያለፈ ሥልጣን የሌላቸው መሆኑ ከኢትዮጵያዊያን አልፎ በውጭ አገራት ታዛቢዎች ሳይቀር የታወቀ ነው። በዚህም ምክንያት ብይኑ በራሱ አዲስ ነገር የለውም። የእለቱን "የችሎት" ውሎ የኢትዮጵያዊያን መነጋገሪያ እንዲሆን ያደረገው ከብይኑ ይልቅ አቶ አንዱዓለም አራጌ የቅጣት ማቅለያ ሃሳብ እንዲያቀርብ የተጠየቀበትን አጋጣሚውን በመጠቀም ያደረገው ንግግር ነው።

አቶ አንዱዓለም "በቅጣት ማቅለያ ሃሳብ" ሰበብ በአገኘው ትንሽ አጋጣሚ ያስተላለፈው መልዕክት ከፍርድ ቤቱ የወራት ድራማ እጅግ በላይ ዋጋ ያለው መልዕክት ነው።

አቶ አንዱዓለም እንዲህ ነበር ያለው

*ያሳለፍነው ግማሽ ምዕተ ዓመት የኢትዮጵያ ሕዝብ ለሰብዓዊ ክብሩና ዴሞክራሲያዊ መብቶቹ የታገለበት ዘመን ነው። ይሁን እንጂ የሰብዓዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶቹ ባለቤት ለመሆን እስካሁን አልታደለም። እኔም በተፈጠርኩበት በዚህ ዘመን ለራሴ፣ ለልጆቼና ለኢትዮጵያውያን ሁሉ ዴሞክራሲና ነፃነት እንደሚገባን በማመን አቅሜ በፈቀደው መጠን ታግያለሁ። ይኼን በማድረጌ በማንም ላይ በክፋት አልተነሳሁም። ይኼን በማድረጌ ህግ ጥሼ አላውቅም። ይኼን በማድረጌ በደሃዋ ሃገሬ ጥቅም ላይ አልተነሳሁም። ይሄን በማድረጌ ፈጣሪዬን፣ የኢትዮጵያን ሕዝብንም ሆነ ህሊናዬን የሚያሳዝን አንዳች ነገር ፈፅሜያለሁ ብዬ አላምንም። ፍፁም ሰላም ይሰማኛል። እኔን እዚህ ያቆመኝ የነፃነት ናፍቆት ነው። በኢትዮጵያ ፍርድ ቤቶችም ፍትህን ለምኜ ስነፈግ ይህ የመጀመሪያዬ አይደለም። ከሳሾቼ እንድጠጣው የሚፈልጉትን የግፍ ፅዋ በፀጋ ከመጠጣት ውጪ ባልፈረፀምኩት ወንጀል ማቅለያ የመጠየቅን አማራጭ ህሊናዬ ስላልተወልኝ አዝናለሁ።*

የአቶ አንዱዓለም አራጌ እያንዳንዱ ዓረፍተ ነገር ከፍተኛ ያለ ዋጋ ያለው መልዕክት ነው። በልበ ሙሉነት "ለራሴ፣ ለልጆቼና ለኢትዮጵያውያን ሁሉ ዴሞክራሲና ነፃነት እንደሚገባን በማመን አቅሜ በፈቀደው መጠን ታግያለሁ" ማለት መቻል መታደል ነው። ለእንዲህ ዓይነቱ ክብር የታደለ ሰው በአፈና ውስጥ ሆኖ እንኳን ውስጣዊ ሰላም አለው። እሱም "ፍጹም ሰላም ይሰማኛል" ነው ያለው።

የአቶ አንዱዓለም መልዕክት የመለስ ዜናዊን ውሳኔ ለማንበብ የተሰሙት ሃሳዊያን ዳኞችን እረፍት የሚነሳ ነገር ነው። በዚህም ምክንያት ነው የመሃል ዳኛው አቶ አንዱዓለምን ለማስቆም የሞከረው። ሆኖም ግን አንዱዓለም ንግግሩን ቀጠለ። "እኔን እዚህ ያቆመኝ የነፃነት ናፍቆት ነው" በማለት የቆመበትን ዓላማ በአንዲት ዓረፍተ ነገር አጠቃሎ አቀረበ። ሃሳዊያኑ ዳኞች ከዚህ በላይ መስማት አልቻሉምና አቶ አንዱዓለምን አስቆሙት። ጋዜጠኛ እስክንድር ነጋና አቶ ናትናኤል ብርሃኑ ደግሞ ተመሳሳይ መግለጫ ይሰጣሉ በሚል ፍርሃት "የቅጣት ማቅለያ" በግልጽ በችሎቱ ውስጥ እንዳያቀርቡ ተከለከሉ። ጋዜጠኛ እስክንድር ነጋ፣ አቶ ናትናኤል ብርሃኑ እና ሌሎችም እድል በማጣታቸው ቢቆጩም መልዕክታቸው በአቶ አንዱዓለም አራጌ አጭር መልዕክት ተጠቃሎ ቀርቧል።

የአቶ አንዱዓለም መልዕክት የተላለፈው ለህሊና ቢሶች የመለስ ዜናዊ አገዛዝ ዳኞች ቢመስልም በዳኞቹ አስመስሎ የተናገረው ለኢትዮጵያዊያን በሙሉ ነው። የአቶ አንዱዓለም ንግግርም የእሱ ብቻ ሳይሆን በእለቱ የመናገር እድል የተነፈጋቸው የመለስ ዜናዊ አገዛዝ ሰለባዎች ጭምርም እንደሆነ እንገነዘባለን።

የመልዕክታቸው ፍሬሃሳብ

*እኛ ኢፍትሃዊነትን፣ አምባገነንነትን፣ ዘረኝነትን ፊት ለፊት በመጋፈጥ እዚህ ድረስ ደርሰናል። እናንተስ ምን እያደረጋችሁ ነው?*

የሚል ነው። መልሳችን ምንድነው?

የኢትዮጵያ ሕዝብ እስከ መቼ ጀግኖቹን ለእስር እየገበረ ይኖራል? ግንባር ቀደም መሪዎቻቸው እየታሰሩባቸው በተቃዋሚ ፓርቲዎች ድክመት እንደምን ማማረር ይቻላል? በየጊዜው አንገታቸውን ብቅ የሚያደርጉ መሪዎቹ እንዲህ እየተቀነደቡ እስከመቼ ይዘለቃል?

ግንቦት 7፡ የፍትህ፣ የነፃነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ በአቶ አንዱዓለም አራጌ መዝገብ ላይ በተከሰሱ ዜጎች ላይ የተሰጠውን ብይን ያወግዛል። የገጠመን ጠላት ፍጹም አምባገነንና ዘረኛ ብቻ ሳይሆን ጨካኝም ጭምር በመሆኑ ትግላችንም ጠላታችንን በሚመጥን መጠን መምረርና መጨከን ይገባዋል ብሎ ያምናል። ስለሆነም ወያኔን ለማስወገድ የተገኙ እና ወደፊትም የሚገኙ አማራጮችን ሁሉ መጠቀም ተገቢ ነው ብሎ ያምናል።

ለእነ አቶ አንድዓለም ጥሪ የግንቦት ምላሽ የሚከተለው ነው።

*የመለስ ዜናዊ አገዛዝ መወገድ ይኖርበታል። የፍልሚያ ስልትም የሚመርጥልን እሱ አይደለም። በተመቸን መንገድ ሁሉ ተጉዘን አገዛዙን እናስወግዳለን።*

በግንቦት 7 እምነት፣ በወያኔ መዳፍ ውስጥ ያሉ ወገኖቻችን በእስር ላይ የሚቆዩበት የስቃይና የመከራ ዘመን የእኛ - ኢትዮጵያዊያን - የመከራና የስቃይ ዘመን ነው።

ኃላፊነቱ ይሰማን። ወያኔን ለማስወገድ ቆርጠን እንነሳ።

**ድል ለኢትዮጵያ ሕዝብ!!!**

.................................................................................................................................................................................................

## በአፋር ክልል ቀይ ሽብር ተጀመረ። በትናንትናው እለት ሁለት የክልሉ ተወላጆች ከእስር ቤት ተወስደው ከተረሸኑ . . . (ከገፅ 1 የዞረ)

በቅርቡም ወያኔ የ 17 ዓመት ታዳጊ በመግደል ለማስፈራራት ከመሞከሩም ሌላ በአፋር ህዝብና በኢሳ መካከል በግጦሽ ምክንያት ይነሱ የነበሩ ግጭቶችን ፖለቲካዊ ገጽታ በመስጠት በአፋር ህዝብ ላይ ጥቃት እንዲሰነዘርበት እያደረገ ነው። ለዚህ ጥቃት ሁኔታዎችን ለማመቻቸትም የአፋር ህዝብ ከዋናው መንገድ በ 5 ኪሎ ሜትር ርቀት ውስጥ መሳሪያ ይዞ እንዳይንቀሳቀስ ከማድረግ ጀምሮ ትጥቅ እስከማስፈታት የዘለቀ ርምጃ እየተወሰደበት ነው በማለት አስረድተዋል።

በመጨረሻም ሊቀመንበሩ የኢትዮጵያ ህዝብ፣ የኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብቶች ጉባኢ (ሰመጉ)፣ ዓለም አቀፍ የሰብዓዊ መብት ድርጅቶችና ዓለም አቀፉ ማህበረሰብ የሚችቹ ጉዳይ በገለልተኛ ወገን እንዲጣራ፣ በእስር ላይ የሚገኙት የዘጠኙ ጉዳይ በህግ እንዲታይና በአጠቃላይ በአፋር ህዝብ ላይ እየተካሄደ ያለው ሰቆቃ እንዲቆም በወያኔ መንግስት ላይ ግፊት እንዲያደርጉ ጥሪ አስተላልፈዋል።

## የወያኔ ጉዳይ ፈጻሚ የሆነው የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት 3ኛ ወንጀል ችሎት በእነ አንዱ ዓለም አራጌ የክስ መዝገብ ላይ . . . (ከገፅ 1 የዞረ)

ወያኔ በቅርቡም በሽብርተኝነት ስም የአንድነት ፓርቲ አባላትን ወደ ዘብጥያ የመወርወር እቅድ እንዳለው መረጃዎች እየወጡ መሆኑን መግለጫው ጠቅሶ ከግል ጋዜጦች ውስጥም የሚታሰሩ ሰዎች ይኖራሉ ሲል አክሏል።

በመጨረሻም ፓርቲው የኢትዮጵያ ሕዝብ፣ በመላው ዓለም የሚገኙ ኢትዮጵያውያንና ዓለም አቀፍ ማህበረሰብ በሀገሪቷ ያለውን አምባገነናዊ ስርዓት ከስልጣን ለማውረድ በሚደረገው ህጋዊ ትግል ከጐኑ እንዲቆሙ ጥሪውን አስተላልፏል።

በፓርቲው ፅ/ቤት ጋዜጣዊ መግለጫውን የሰጡት ዶ/ር ሃይሉ አርአያ፣ አቶ ግርማ ሰይፉ፣ አቶ አስራት ጣሴና አቶ ዳንኤል ተፈራ ናቸው፡፡

በተመሳሳይም የፓርቲው ሊቀመምበር ዶ/ር ነጋሶ ጊዳዳም ለፓርቲው አባላትና ለኢትዮጵያ ህዝብ ከጀርመን በላኩት አጭር የጽሁፍ መልእክት ፍርድ ቤቱ የሰጠው ውሳኔ የህገ-መንግስቱን አንቀጽ 29፣ 30 እና 31 የሚጥስ በመሆኑ ማዛናቸውን ገልጸዋል፡፡

ዶር ነጋሶ ጊዳዳ በመለስ ዜናዊ ሞግዝትነት ሥር የተሰጣቸውን የአገሪቱ ፕሬዝዳንትነት ሥልጣን ላይ ለመቆየት ሲሉ ለወያኔ ታማኝ አሽከር ለመሆን ባለመፈቀዳቸው ሊያገኙ የሚገባ ጡረታና ጥቅማጥቅሞች የተነጠቁ አገር ወዳድ የነጻነትና የፍትህ ታጋይ መሆናቸው ይታወቃል። በአህኑ ሰዓት ጀርመን አገር የሚገኙት ዶር ነጋሶ አግራቸውን ኦፐራሲዮን ህክምና ካልተደረገለት በቀር የመቆረጥ አደጋ ሊገጥመው እንደሚችል በሃኪም እንደተነገራቸው የአንድነት ፓርቲ ገልጾ ለህክምና የሚያስፈልጋቸውን 8 ሺ ኢሮ ህዝብ እንዲያውጣላቸው ተማጽኖአል። የግንቦት 7 ድምጽ ማንኛውም አገር ወዳድ ኢትዮጵያዊ እንደሌሎች የወያኔ ሹሞች አገራቸውንና ህዝባቸውን ዘርፈው መከበር ሲቺሉ ለእውነት ሲሉ የድህነት ኑሮ ለመረጡት ለእኚህ ታጋይ ሰው የእርዳታ እጁን እንዲዘረጋ ወገናዊ ጥሪው ያቀርባል።

## ሁሉ ሠላም ነውን ?

ኢትዮጵያ እንደ እንቁ የከበረ፤ እንደ ማር ወተት የጣፈጠ ታሪክ ያላት አገር ነበረች። ዜጎቿም በየሄዱበት የትልቅ አገር ህዝቦች ተብለው ተከብረው አንገታቸውን ቀና አድረገው የሚኖሩ ነበሩ። እስከ ቅርብ ግዜ ድረስ ኢትዮጵያዊ በሚሄድበት አገር ሁሉ "ኢትዮጵያዊ ነኝ" ማለት ብቻ በቂ ሁኖት ያለፓስፖርት እንዲገባ ይፈቀድለት ነበር። ብዙ ህንዳዊያን ወደ አውሮፓ እና አሜሪካ መሻገር ከፈለጉ ኢትዮጵያ ሂደው የኢትዮጵያዊያንን መታወቂያ ለመያዝ ብዙ ይደክሙ ነበር። ትልቁ ሰው ማንዴላ ለመጀመሪያ ግዜ ኢትዮጵያዊ አብራሪ ሲያዩ በእጅጉ ተደነቀው እንደነበረ በመጽሃፋቸው አስፈረውታል።

ከዚህ የምንማረው ኢትዮጵያችን ትልቅ አገር፤ ዜጎቿም የተከበሩ የሰው ዘሮች መሆናቸውን ነው።

መቸስ ብዙ የሚደነቅ ታሪክ እና ገድል ቢኖረንም አሁን ሁሉም በነበር ቀርቷል። ትልቅ ህዝብ ነበርን።የትልቅ ታሪክ ባለቤት ነበርን። ዜጎቿ ሁሉ በየሄዱበት ተከብረው አንገታቸውን ቀና አድርገው የሚኖሩ ነበሩ። እንዲያውም ወደ ውጭ አገር መሄድ እንደ ግዞት የሚቆጠርባት አገርም ነበረች።

ዛሬ ያለንን ዋና ዋና እሴቶቻችን በሙሉ ተወስዶብን ባዶ እጃችንን ልንቀር ጥቂት ግዜ ይቀረናል።የነበረን እንዳልነበረ ሁኖ ኢትዮጵያዊያ ድቅድቅ ጭለማ ውስጥ እንድትኖር ለማድረግ ዘረኞቹ ሌት ተቀን እየማሰኑ ነው። ትውልዱ ዘመኑ የደረሰበትን ቴክኖሎጂ እንኳ እንዳይጠቀም ለማድረግ ህግ አውጥተዋል። ስካይፒ መጠቀም 15 ዓመት የሚያሳስር ወንጀል ነው ተብሏል። በዚህ ዘመን በኢትዮጵያ ውስጥ እንዲህ ያለ ህግ መውጣቱ አገሪቷ የገባችበትን የውረደት አዘቅት የሚያመላክት እንጂ አገራችን መዘመኗን የሚያሳይ አይደለም።

አገሪቷ እንዲህ በውረድት አዘቅት ውስጥ እያለች "ሁሉ ሰላም" ነው የሚሉ አሉ። "ምን ውርደት ምን መከራ አለ "ብለው የሚጠይቁም አሉ። እንዲህ ላሉ ውረደታቸው ላልተከሰተላቸው ወገኖች እነሆ መልእክታችን። ወደ ውጭ አገር መሄድ እንደግዞት በሚቆጠርባት አገር ውስጥ ዜጎች ክረምትና በጋን ሳይለዩ በተገኘው አጋጣሚ እና በተገኘው መንገድ እግራቸው ወደ መራቸው የመሰደዳቸው ነገር ለኢትዮጵያዊያን ውረደት ነው። ባለፈው ሰኔ ወር ብቻ 60 የሚሆኑ ወጣት ኢትዮጵያዊያን በጀልባ ተሳፍረው ወደ ደቡብ አፈሪካ ሲሰደዱ ውሃ ብልቷቸዋል። በዚሁ ወር ሌሎች ወደ 42 የሚሆኑ ደግሞ እንደ እቃ በመኪና ጀርባ ተጭነው ሲጓዙ አየር አጥሯቸው ሙተው ሜዳ ላይ ተጥለው ተገኝተዋል። ይህ በወገኖቻችን ላይ የደረሰው ስቃይ ለእኛ ለቋሚዎቹ ህመማችንና ውርደታችን ነው።

ባንድ ወቅት አገራችን ፍትህ የነገሰባት የተከበረች አገር ነበረች። ዛሬ ያ ፍትህ የለም።በአገራችን ፍትህ መጥፋቱም ለዜጎች ስደትና በየደረሱበትም ለመዋረዳቸው ዋነኛው ምክንያት ነው። አገር ውስጥ የቀሩትም ዜጎች በሃሰት ተወንጅለው፤ በሃሰት ተመስክሮባቸው የሞት ፍርድ እየተፈረደባቸው ነው። ዜጎች ዘር ሃረጋቸው እየተመዘዘ የመከራ እንጀራን እንዲበሉ የመከራ ጽዋንም እንዲጠጡ እየተደረገ ነው። እንዲህ ያለው ኢ-ፍትሃዊ ነገር የሚፈጸምባት አገር ውስጥ የሚኖር ማሰብ የሚችል ዜጋ "ሁሉ ሠላም ነው" ሊል አይችልም። ዛሬ በኢትዮጵያችን ውስጥ የፍትህ ያለህ ማለት አሸባሪነት ሆኖ እየተቆጠረ ባለበት በዚህ ዘመን "ችግር የለም ሁሉ ሠላም ነው" ማለት አይቻልም።ከሰሞኑ አሸባሪ ናቸው ተብለው የተፈረደባቸው ንጹሃን ዜጎች ከቶ ምን ይሆን ጥፋታቸው? የሠላም ምንጭ የሆኑት ነጻነት!! ፍትህ!! እኩልነት!! ይሁን ማለታቸው አይደለምን? ነጻነት ብሎ የጠየቀን ዜጋ አሸባሪ ነው የሚል መንግስት ነኝ ባይ በአገሪቷ ላይ መኖሩስ ለአገራችን የውረደቷ ምልክት አይደለምን ? እንዲህ ያለ አገር ውስጥ የሚኖርስ እንደምን ሁኖ "ሁሉ ሠላም ነው" ሊል ይችላል ?

በኢትዮጵያችን ውስጥ ህግ ቂም መወጣጪያ እና ዜጎችን ማፈኛ መሳሪያ በመሆኑ ኢትዮጵያዊያ እና ኢትዮጵያዊያን ለብዙ መከራ ተዳርገው እያየን ነው። ህግን ከለላ አድርገው አገሪቷን የሚያራቁቱ፤ የአገሪቷን ጥቅም አሳልፈው ለባእዳን የሚሰጡ ኃይሎች የአገሪቷ ህግ አውጪዎች ሁነው ራሳቸውን በመሰየማቸው አገሪቷ ሠላም እርቋታል። ዛሬ በአዋሳ የንጹሃን ደም የሚፈሠው ህግና ህግ አስከባሪው ቂም መወጣጪያ መሳሪያ በመሆናቸው ነው። ዛሬ ጋምቤላ ውስጥ የምንሰማው ድምጽ ሠላም ያለው አይደለም። የአገርን ጥቅም አሳልፎ ለባእዳን የሚሰጥ ቡድን የአገር ህግ አውጪ ሁኖ ዜጎችን ለመበቀል በመቆሙ በጋምቤላ ሠላም ጠፍቷል። በዋልድባ እና በአንዋር መስኪድ ውስጥም የምናየው ህግን ከለላ አድረገው ዜጎችን ለመጉዳት ያሰፈሰፉ ነውረኞች በስልጣን የመቀመጣቸው ውጤት ነው። በአፋር እና በኦጋዴን የምናየው የዘር ማጥፋት ወንጀልስ የሚፈጸመው ህግን ቂም መወጣጪያ አድርገው በሚጠቀሙ ቡድኖች አይደለምን ?

ወገኖቻችን በኢትዮጵያችን ሁሉ ሠላም አይደለም። ብዙ ችግሮች አሉ። ብዙ ሮሮዎች በሁሉም አቅጣጫዎች እየተሰሙ ነው። የዜጎች ደም በከንቱ እየፈሰሰ ነው። እናቶች ደረታቸውን እየደቁ እያለቀሱ እያየን ነው። በዘመነ ህወሃት ችግሮቻችን ፈረጀ ብዙ ናቸው። ሁሉም ሠላም አይደለም።

የዛሬይቷ ኢትዮጵያ የአሳዳጆችና የተሰዳጆች ስፍራ ሁናለች።ጥቂት ዘረኞችና ግፈኞች አሳዳጆች ብዙሃኑ ደግሞ ተሰዳጆች ወይም ደግሞ መሰደድን የሚመኙ ሁነው የሚኖሩባት ሥፍራ ነች ኢትዮጵያ። ይህች ትልቅ የነበረች አገራችን፤ ይህች በዓለም ህዝብ ፊት ጥሩ ዝና የነበራት አገራችን ዛሬ በጥቂት ዘረኞችና ምንም አገራዊ ኃላፊነት በማይሰማቸው ቡድኖች እጅ በመውደቋ የነበራትን ክብር አጥታ ለመፈራረስ አደጋ ላይ ያለች አገር ለመባል በቅታለች።በዘረኞች እጅ ያለች አገር ያተረፈችው ይህን የመሰለውን አለመረጋጋት እንጂ ሠላምን አይደለም።

ግንቦት ሰባት የፍትህ የነጻነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ ለኢትዮጵያችን ውርደት ተጠያቂዎቹ ትግራይን "ነጻ" እናወጣለን ብለው የተነሱት ዘረኞች ናቸው ይላል። እነዚህ ጥቂት ዘረኞች አጥንትና ደማቸውን ቆጥረውና ተደራጅተው ኢትዮጵያዊያንን ለስደት፤ ለእስራት፤ ለርሃብና ለጦርነት ዳርገዋል።እነዚህ ዘረኞች የአገሪቷን ስልጣን ከተቆናጠጡ ግዜ ጀምሮ የኢትዮጵያ መገለጫ እስራት፤ ስደት፤ ርሃብና የእርስ በርስ መጠላላት ሁኗል። የእነዚህ ቡድኖች ክፋት ወሰነ ያለው አይመስልም።እንግዲህ እነዚህ ዘረኞች ደምና አጥንታቸውን ቆጥረው ተሳስረው አገሪቷን ሲያፈርሱ እያየን ዝም ማለት አይገባንም።አልበርት አንስታይን ***"ዓለማችን የምትጠፋው ክፉ በሚያደርጉት ሳይሆን ክፉ ሲያደርጉ እያዩ ዝም በሚሏቸው ሰዎች ነው"*** እንደሚለው አገር ስትጠፋ እያዩ ሁሉ ሠላም ነው ማለት ከአገር አፍራሾቹ ጎን መቆምን መምረጥ ነው።

ዛሬ ህወሃቶች በብሄረሰቦች መካከል ጥላቻን እየዘሩ ነው።የዘሩት የጥላቻ ዘር መቼ በቅሎ ፍሬ እንደሚይዝ አናውቅም።ሆኖም ግን የተዘራው የጥላቻ ዘር በቅሎ ፍሬ አያፈራም ማለት ደግሞ አይቻልም። ዘሩ በቅሎ ፍሬ ያፈራ እለት ግን ለማንም በጎ ነገር አይሆንም። በወንድማማቾች መካከል ጠብን የሚዘራ ቡድን በራሳችን ላይ ሁኖ አገሪቷን ሲያፈራርስ እያየን ሁሉ ሠላም ነው ማለት ተገቢ አይደለም። ማህተመ ጋንዲ እንዲህ ይሉናል"***መጥፎ ስርዓትን በጣም ጥሩ አድርገህ የምታጠናክረው ትዕዛዛቱን እና አገዛዙን እሺ ብለህ ስትቀበል ነው፡፡ መጥፎ ስርዓት እንዲህ ዓይነት ታዛዥነት አይገባውም፡፡ ለዚህ ዓይነቱ ስርዓት መታዘዝ ማለት ለጥፋቱ ተባባሪ መሆን ማለት ነው፡፡ ማንኛውም መልካም ሰው የተበላሸ ስርዓትን በሙሉ እስትንፋሱ መቃወም አለበት"***

ዛሬ ለዘረኛው ቡድን ድርና ማግ ሁነው የሚያገለግሉ ግለሰቦች አሉ። በወገኖቻችን ደምና አጥንት ላይ ህንጻ የሚገነቡም አሉ። ወገኖቻችን ሲያለቅሱ የሚሳለቁም አሉ። ባህር ተሻገረው ዜጎችን የሚያሳድዱም አሉ። የግንቦት ሰባት ንቅናቄ እንዲህ ዓይነት ነውረኞችን ዝም አይላቸውም። ነገ የነጻነት ጎህ ሲቀድ በኢትዮጵያን ፊት በኩራት ለመቆም ትቸገራላችሁ፤ ሥራችሁም የሚያሳድዳችሁ ይሆናል፤ አገርን የሚበድል ጠላት በተነሳ ግዜ ከጠላት ጎን መቆምን መርጣችኋልና ወየውላችሁ፤ የህዝቡን ትእግስት እንደፍርሃት ቆጥራችሁታልና ወየውላችሁ፤ ጭካኔያችሁን እንደ ጀግነት ቆጥራችሁታልና ወየውላችሁ እያለ ከወዲሁ ያስጠነቅቃል።

አገራችን አሁን ባለችበት ደረጃ ስትዋረድ እየታየ "ሁሉ ሠላም" ነው ማለት ትክክል አይደለም።ዜጎች በራሳቸው ላይ ጋዝ አርከፍክፈው ተቃጥለው ሲሞቱ እየታየና እየተሰማ ምንም "ክፉ ነገር የለም ሁሉ ሠላም ነው" ማለት ነጻነቱን ተነጥቆ ለሚንገላታው ህዝብ ፍቅር ማጣት እንጂ ሌላ ምንም ሊባል አይችልም።እንደ እንቁ ከብረው ይኖሩ የነበሩ ኢትዮጵያዊያን ዛሬ ዘመን ፊቱን አዙሮባቸው በየበረሃው እና በየባህሩ ቀልጠው ሲቀሩ እያየ "ሁሉ ሠላም ነው ምንም ችግር የለም" ማለት የጨዋ ሰው ልማድ አይደለም። በህወሃት ሰዎች አማካኝነት ወደ አረብ አገር በሚሰደዱ ሴቶች እህቶቻችን ላይ የሚደርሰውን ስቃይና ውርደት ለምን ብሎ የሚጠይቅ መንግስት የሌለን አገር ዜጎች ሁነን ሳለ እንደምን ሆኖ "ሁሉ ሠላም ነው ምንም ችግር የለም" ለማለት እንችላለን? ሴቶች እህቶቻችን ወደ አረብ አገር ለግርድና ሲጋዙ ና በተቃራኒው አረቦች ወደ እኛ አገር ለግብርና ሲመጡ እያየን "ሁሉ ሠላም ሁሉ ደህና" ማለት አያሳፍርምን ?

መልዕክታችንን ለማጠቃለል ያክል ጥቂት ዘረኞች አገሪቷን በሁሉም አቅጣጫ ሲያዋርዱ እያየ "ችግር የለም ሁሉ ሠላም ነው" እያለ በወገንና በአገር ኪሳራ የግል ጥቅሙን የሚያሳድድ ሁሉ ከህዝብና ከሂሊና ፍርድ እንደማያመልጥ ልናስታውስ እንወዳለን ;;

ድል ለኢትዮጵያ ህዝብ!!!!
እግዚአብሄር ኢትዮጵያን ይባርክ !!!

## የደቡብ ክልል መስተዳደር ዋና ከተማ በሆነቺው አዋሳ በተነሳው ግጭት በሰው ህይወትና ንብረት ላይ አደጋ መድረሱ ቀጥሎአል

በደቡብ ክልል ዋና ከተማ አዋሳ ላይ በተነሳው ውዝግብ ላለፉት 2 ሰማንታት ባለማቋረጥ እየተከሰተ ያለው ግጭት ተባብሶ ባለፈው እሁድ ምሽት በፌደራል ፖሊስና በህዝቡ መካከል በተነሳ ግጭት 1 ሰው ሲገደል ሁለት ደግሞ መቆሰላቸውን ከአካባቢው ከደረሰን ዜና ለማወቅ ተችሎአል።

እንደ ዜና ምንጮቻችን ዘገባ ለሰው ህይወት ቅጥፈት ምክንያት የሆነው ግጭት የተነሳው በአዋሳ ከተማ ወልደአማኑኤል ዱባለ እየተባለ በሚጠራው አደባባይ አካባቢ በተካሄደ አንድ የሰርግ ስነስርአት ላይ የሲዳማ ወጣቶች በሲዳምኛ እየጨፈሩ ሙሽሮችን ለመቀበል ሲሄዱ የወያኔ ፌደራል ፖሊስ አባላት በከፈቱት ተኩስ ነው። ፍጹም ሰላማዊ የሆኑ ዜጎችን ለማሸበር ሲባል ብቻ ሆን ብለው በህዝቡ ላይ ተኩስ በከፈቱት የወያኔ ፌደራል ፖሊሶች ድርጊት የተበሳጨው የአካባቢው ነዋሪ ንደቱንና ብስጪቱን ለመግለጽ ወደ ፖሊሶቹ ድንጋዮችን ሲወረውር ታይቶአል።

ምንም አይነት መሳሪያ በእጁ ያልያዘውን ሰላማዊ ህዝብ በሃይል ጸጥ ለማሰኘት እስከ አፍንጫው ታጠቆ በከተማው የሰፈረው የወያኔ ሠራዊት ህዝቡን ለማስፈራራትና ለማሸማቀቀ ሌሊቱን በሙሉ ከተማውን በጥይት እሩምታ ሲያውክ ከማደር አልፎ በትናንትናው ዕለትም አልፎ አልፎ የተኩስ ድምጽ ሲያሰማ እንደዋለ ታውቆአል።

ወያኔ በከፋፍለህ ግዛ ፖሊሲው በሰላም አብሮ የሚኖረውን ህዝብ በማጋጨት የሥልጣን ዕድሜውን ለማራዘም ከሚንቀሳቀስባቸው የአገሪቱ ከተሞች አንዱ በሆነቺው አዋሳ የመለስ ዜናዊ ሠራዊት ከአሁን በፊት የበርካታ ንጹሃን ዜጎችን ደም በከንቱ ያፈሰሰ መሆኑ ይታወቃል።

የአዋሳ ህዝብ የወያኔን መሰሪ ፖሊሲ በተደጋጋሚ ሲቃወም የኖረ ህዝብ በመሆኑ በአሁኑ ጊዜ በመላው አገሪቱ በሰፈነው ከፍተኛ የኑሮ ውድነት፤ ሥራ አጥነትና፤ የፖለቲካ አፈና ምክንያት ህዝቡ ሆ ብሎ ሊነሳ ይችላል በሚል ስጋት በከተማዋ ከባድ መሳሪያዎችን የታጠቁ የፌደራል ፖሊስ አባላት በብዛት ተሰማርተው ከተማዋን በማጨናነቅ ላይ መሆናቸውን የአይን እማኞች ይናገራሉ።

የኢትዮጵያ ሳታላይት ቴለቪዥን ኢሳት በአዋሳ የሚገኝ የዩኒቨርስቲ ተማሪዎች፣ የግብርና ሰራተኞች፣ መምህራን፣ የክልሉ ፖሊስ ተወካዮች፣ የምክር ቤት አባላትና እና ሌሎችም ከ 300 በላይ የሚሆኑ ወጣቶች ባለፈው ቅዳሜ በአዋሳ ከተማ በህቡእ ተሰባስበው የሲዳማ ወጣቶች ንቅናቄ የሚል ድርጅት መመስረታቸውን መዘገቡ ይታወሳል።

## ወያኔ የዋልድባን ገዳም ለማፍረስ የወጠነውን ዕቅድ የተቃወሙ የገዳሙን መነኮሳት እያሳደደ መሆኑ ተዘገበ

የዋልድባ ሰቋር ኪዳነ ምሕረት ገዳም አራት መነኮሳት ባለፈው ቅዳሜ በመንግስት ታጣቂዎች ተይዘው መወሰዳቸውንና ገዳሙም ከሰሜን ጎንደር ዞን በተላኩ በርካታ የፌዴራል ፖሊሶች ተከቦ እንደሚገኝ “ደጀ ሰላም” የተሰኘው ድረገጽ በዝርዝር ዘገበ።

እንደ ዜናው ዘገባ በሱባኤ ላይ የነበሩ በርካታ መነኮሳትም በፖሊሶች ዱላ ተደብድበው እንዲበተኑ መደረጋቸው ታውቋል። ከገዳሙ ከተወሰዱት አራት መነኰሳት መካከልም ሶስቱ አባ ኀይለ ኢየሱስ፣ አባ ግርማይ፣ አባ ገብረ እግዚአብሔር ተብለው የሚጠሩ ሲሆን፣ የአራተኛውን መነኩሴ ስም ግን ለጊዜው ለማወቅ አልተቻለም፡፡

የወልቃይት ስኳር ልማት ፕሮጀክት በገዳሙ ህልውናና ክብር ላይ በጋረጠው ስጋት ሳቢያ የሰቋር ኪዳነ ምሕረት ማኅበረ መነኰሳት ግንቦት 22 ቀን “ኑ፣ ታቦቱን፣ ቅርሱን ተረከቡ፤ እኛ እንፈልሳለን ወይም ወደ በርሓ እንሰወራለን” የሚል ጥሪ ለምእመኑ ማስተላለፋቸው የሚታወስ ሲሆን፣ ይህን ተከትሎም በዓዲ አርቃይ ወረዳ ሳንቅ፣ ዛሬማ፣ ያሊ፣ የጥራይና፣ ጅሮሰ፣ ነብራና ፍድቃ የተሰኙት ቀበሌዎች ነዋሪዎች ዛሬማና ሰቋር ላይ በመሰብሰብ ተቃውሟቸውን አጠናክረው መቀጠላቸው ታውቋል።

ተቃውሟቸውን በሰላማዊ መንገድ እየገለፁ ያሉ በርካታ ወጣቶችም ተይዘው እየታሰሩና ድብደባም እየፈፀመባቸው እንደሆነ የሚገልፀው የደጀሰላም ዘገባ፣ በአካባቢው እያየለ የመጣውን የምዕመናኑን ተቃውሞ ለማርገብ የክልሉን ፕሬዚዳንት አያሌው ጎበዜን ጨምሮ፣ የቤተክርስቲያኗ መንበር ላይ ተቀምጠው የመንግስትን አቋም የሚያራምዱ የሃይማኖት አባቶች በተደጋጋሚ ያደረጉት ጥረት ሊሳካ እንዳልቻለ ይገልፃል።

እነዚሁ የመንግስትና የአቡነ ጳውሎስ ተወካዮች መነኮሳቱን፣ “ሃይማኖትን ሽፋን እያደረጋችሁ የፖለቲካ ዘመቻ ታደርጋላችሁ፤ የፀረ ሰላም፣ ፀረ ልማት ተቃዋሚ ፓርቲዎች ሰለባ ሆናችኋል፤ የእነርሱን ድምፅ ነው የምታስተጋቡት፤” እያሉ በግልጽ ከመዛለፋቸውም በተጨማሪ “ብትስማሙና የሸንኮራው ልማት ቢለማ ምናለበት?” በማለት በተደጋጋሚ ለማግባባት ሞክረዋል። ሆኖም መነኰሳቱ በበኩላቸው “በልቅሶ ነው ያለነው፤ ዐፅም ወጥቶ ውኃ አይቆምም፤ ቤተ ክርስቲያን እየፈረሰ በሚለማ ልማት አንስማማም፤ ዋልድባ ቅንጣት ያህል አትነካም›፤ ይህ የሃይማኖት ጉዳይ እንጂ የፖለቲካ አይደለም” በማለት ያላቸውን አቋም በግልጽ አስረድተዋል።

የዋልድባ ገዳም የሚገኝባቸው ሦስቱ አህጉረ ስብከቶች፣ እንዲሁም የወረዳ ቤተ ክህነት ጽ/ቤቶች የገዳሙን ሕልውና እየተዳፈረ ያለውን የመንግሥት ውሳኔ በመቃወም ከሌላው የቤተክርስቲያኗ ተቆርቋሪዎች ጎን ያለመቆማቸው ያሳዘነው ምእመኑ ከዘንድሮው ዓመት ጀምሮ “የነፍስ ዐሥራት በኵራት” ሲል የሚጠራውን መባዕና የሰበካ ጉባኤ አስተዋፅኦ እንደማይከፍል ለወረዳ ቤተ ክህነት በጻፈው ደብዳቤ መፃፉን ደጀሰላም በዚሁ ዘገባው ጠቅሷል፡፡

ይኸው ዘገባ አያይዞ እንደገለፀው ከሆነም፣ የዛሬማ ወንዝ ላይ ሊሰራ የታቀደውን የግድብ ሥራ ተረክቦ ሲመራ የቆየው ሱር ኮንስትራክሽን ሥራውን አቋርጦ በመውጣት በምትኩ ለአንድ የቻይና ተቋራጭ ተሰጥቷል። ለዚህ ምክኒያት ይሆናሉ ተብለው ከተጠቀሱት ነገሮች ውስጥ፣ ቁፋሮው የሚካሄድበት ቦታ ከመሬት በሚፈልቅ ውኃ እየተሞላ ማስቸገሩ፣ እንዲሁም የምእመኑ ተቃውሞ ያሳደረው ግፊት ዋነኞቹ ናቸው። የዛሬማ ግድብ ስራ ንድፍ የተዘጋጀው በትግራይ ውኃ ሥራዎች ዲዛይንና ሱፐርቪዥን ሲሆን፣ የግንባታ ስራውን የሚያከናውነው ደግሞ የትግራይ ውኃ ሥራዎች ኮንስትራክሽን ነው።

የኢትዮጵያ ሳተላይት ቴለቪዥን ኢሳት ደጀሰላም ያወጣውን ዘገባ ተከትሎ ሁኔታውን ለማጣራት ወደ አካባቢው ደውሎ ወያኔ ገዳሙን ለማፍረስ የሚያደርገውን ጥረት የተቃወሙና ለተለያዩ መገናኛ ብዙሃን መረጃ ያቀበሉ መነኮሳት እየተከዋከቡ መሆኑን ማረጋገጡን በትናትናው ዕለት የዜና ዘገባው አስታውቆአል።

## ሰሜን አሜሪካ ዉስጥ ዋሺንግተን ዲሲ ና ዳላስ ዳላስ በኢትዮጵያዉያን አሸበረቀች ዲሲ የሰዉ

. . . (ከገፅ 3 የዞረ)

የኢትዮጵያዉያንን መሰባሰብ የማይወደዉ ዘረኛዉ መለስ ዜናዊ ESFNA በሚል ምህፃረቃል የሚታወቀዉንና 29 አመት ዕድሜ ያስቆጠረዉን ድርጅት ቢቻል ለመቆጣጠር ባይቻል ደግሞ ለማፍረስ በሚሊዮን የሚቆጠር ዶላር አፍስሷል። ሙከራዉ አልሳካ ሲለዉ ESFNA በሚባለዉ ስም ላይ One የሚልቃል በመጨመር የራሱን የክርስትና ስም ሰጥቶ በእጅ አዙር ሊቆጣጠረዉ ሞክሯል። ሆኖም ቆራጥ የኢትዮጵያ ልጆች ይህንን የቅጥፈት እርምጃ በአፋጣኝ ወደ ፍርድ ቤት በመዉሰድ በአብነትና በኣላሙዲ ተላላኪዎች ላይ ታላቅ ድል ተቀዳጅተዋል። ኢትዮጵያ ዉስጥ ፍርድ በገንዘብ መግዛት የለመዱት እነአብነት ገ/መስቀልም ፍትህ በገንዘብ በማይገዛበት በነፃዉ ፍርድ ፊትዉ ርዳታቸዉን ተከናንበዋል። እነዚህ አይናቸዉን በጨዉ ያጠቡ ጋጠወጦች ግን AESAONE የሚል አዲስ ድርጅት በመፍጠር የዘንድሮዉ የኢትዮጵያዉያን የስፖርት በዐል ዲሲ ዉስጥ ነዉ ብለዉ ማስወራት ጀመሩ። ይህንን እኩይ የከፋፋይነት ስራቸዉን እዉነት ለማስመሰልም ባለ አራት ኮከብሆቴል፤ 80 ሺ ተመልካች የሚይዝ ስታዲዮምና በመቶሺዎች ዶላር የሚያስከፍሉ አሜሪካዉያን ዘፋኞችን ተከራዩ። ሆኖም አገራቸዉን የሚወዱ ቆራጥ ኢትዮጵያዉያን በወሰዱት የማያዳግም እርምጃ በዚያ 80ሺ ሰዉ በሚይዘዉ ስታዲዮም ዉስጥ ተገኝተዉ ሁለት መቶ ሺ ዶላር የተከፈላቸዉን ዘፋኞች ያዳመጡት አብነት ገ/መስቀልና ትቂት ሆዳሞች ብቻ እንዲሆኑ አደርገዋል። ከሁለት መቶ ሺ በላይ ኢትዮጵያዉያን በሚኖሩባት ዋሺንግተን ዲሲ ዉስጥ የወያኔ ተላላኪዎች ባዘጋጁት በዐል ላይ ከተገኘዉ የተመልካች ቁጥር ይልቅ ከስታዲዮሙ ዉጭ ቆሞ ተቃዉሞዉን በመፈክር ያሰማ የነበረዉ ህዝብ ቁጥር እንደሚበልጥ ሁኔታዉን በአካል ተገኝቶ የተከታተለዉ የግንቦት 7 ዘጋቢ ከስፍራዉ ባስተላለፈዉ ዘገባ ገልጾልናል።

ዘረኛዉ መለስዜናዊ ባለፈዉ ግንቦት ወር ሮና ልድ ሬገን አዳራሽ ዉስጥ የተለመደ የቅጥፈት አንደበቱን ሲከፍት አንገቱን ያስደፉት ኢትዮጵያዉያን ዛሬ ደግሞ እዚያዉ ዋሺንግተን ዲሲ ዉስጥ የመለስ ተላላኪዎችና አጎብዳጅ ቡችሎች በህዝብ ገንዘብ የደገሱትን መጠነ ሰፊ ድግስ እነሱ አራሳቸዉ ብቻ እንዲበሉት በማድረግ ምንግዜም ቢሆን ለዘረኞችና ለባንዳዎች የማያጎበድዱ አገር ወዳዶች መሆናቸዉን በተግባር አስመስክረዋል። መለስ ዜናዊና ግብረአበሮቹም በአንድ ወር ዉስጥ ለሁለተኛ ግዜ ዉርደታቸዉን ተከናንበዋል። በዳላስ እየተካሄደ ያለው የሰሜን አሜሪካ የኢትዮጵያዊያን እግር ኳስ ውድድር የፊታችን ዕሁድ በታላቅ ሥነሥራአት ይጠናቀቃል ተብሎ ይጠበቃል።

**የግንቦት 7 ድምጽ ሬዲዮ የሥርጭት ሞገድ እንደሚከተለው ነው።**

**መካከኛ ሞገድ**:- በ 358 MB, በ 837 kHz
**አጭር ሞገድ**:- በ 31 MB በ 9700 KHz
**በ 41 MB በ 7185, በ 7175 በ 7160 እና በ 7120 KHz**
**በ 49 MB በ 5980 KHz እና በ 60 MB 4760 GHz**

ላይ ዘወትር ማክሰኞ እና ሐሙስ ከጠዋቱ 2፡30 እስከ 3፡00 ሰዓት በድጋሜም ከሰዓት በኋላ 11፡30 እስከ 12፡00 ሰዓት እንዲሁም ዘወትር ቅዳሜ ከጠዋቱ 3፡00 እስከ 3፡30 ሰዓት እንዲሁም ከሰዓት በኋላ ከምሽቱ 11፡30 እስከ 12፡00 ሰዓት የሚደመጥ መሆኑን እየገለጽን በወያኔ አፈና ምክንያት ሬዲዮናችን የመደመጥ ችግር ከገጠመው በድብዳቤ፣ **በስልክ** ወይም **በኢሜል** በንቅናቀያችን አድራሻዎች እንድታስታውቁን እንገልጻለን።

ማሳሰቢያ:- ሰዓቱ በኢትዮጵያ የሰዓት አቆጣጠር ነው።

**ውድ አንባቢዎቻችን**

ለፕሮግራማችን ይበጃል ያስተምራል ብላችሁ የምታሰቡትን መጣጥፋችሁን ለሬድዎን ክፍላችን ወይም ለሳምንታዊው ጋዜጣ ክፍል በሚከተለው የኢ-ሜል አድራሻ ትልኩልን ዘንድ የአክብሮት ግብዛችንን እናቀርባለን። g7radio@ginbot7.org